## 3. አማኞች የመንግሥቱ ዜጎች ሶስተኛው መስርታውያን ናቸው።

የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎች በክርስቶስ በኩል ከጨለማው ስልጣን አገዛዝ የዳኑ እና በእግዚአብሔር አገዛዝ ስር ያሉትን አማኞች ያቀፈ ነው። የእርሱን በጎነት ለመናገር የተመርጠ ቅዱስ ህዝብና የንጉስ ካህናት የሆኑ የአማኞች ስብስብ ነው።ቆላ 1፡13-14 1ኛ ጴጥ 2:9፡

## 1. የመንግሥቱ ዜግነት ፍቺ

- የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ መሆን ማለት፡- በክርስቶስ የተሰበከውን የእግዚአብሔር መንግስት የምስራች በመቀበል **አዲስ ማንነት መያዝ** እና **በታማኝነት ለእርሱ በመግዛት መኖር** ማለት ነው።ይህ ዜግነት በመልካምድራዊ ወሰን ወይም በፖለቲካ ርዕዮት ከሚገልጸው ምድራዊ ዜግነት የተለየ **ነው**።**የእግዚአብሔር መንግሥት ዜግነት መንፈሳዊ ነው**።የሚገኘውም በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እና በመንፈስ ዳግም በመወለድ ብቻ ነው። **ዮሐንስ 3፡3, 5**።ቲቶ 3:3-7 1ጴጥ 1:22-23

## 2.የመንግስቱ ዜግንት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት

- የእግዚአብሔር መንግሥት ዜግነት ከምድራዊ ኃይል ወይም ሥርዓት ጋር የተያያዘ ሳ ይሆን **ከክርስቶስ የጽድቅ ግዛት ጋር የተያያዘ ነው።** ዮሐ 18:36፡ **ኢየሱስ መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም በማለት ይህን አረጋግጦል።**

- ስለዚህ አማኞች በዋነኛነት የሚገለጹት በምድራዊ ብሔራቸው ሳይሆን **የእግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግሥት አባል በመሆን ነው**።**ፊል 3:20 አገራችን ግን በሰማይ ነው ፥** ከዚያም የሚመጣውን መድኃኒት እርሱንም **ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን** ።በማለት ቅዱስ ቃሉ ይህን እውነት ያረጋግጣል።

➢ **ወደ** **መንግስቱ**
**ህጋዊ ሽግግር የሚከናወነው በድነት ጊዜ ነው። ከሰይጣን አገዛዝ ነጻ ወጥቶ** ወደ **ወደ እገዚአብሔር አገዛዝ በደሙ የኀጢአት ስርየት በማግኘት** ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግስት መፍለስ ወይም ህጋዊ ሽግግር ማድረግ ነው። ። ቆላ 1:13 እርሱ ከጨለማ ግዛት አዳነን፥ ወደ ፍቅሩም ልጅ መንግሥት አፈለ ሰን።

➢ የመንግስቱ ዜግነት ማለት ደግሞ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ መካተት ማለት ነ ው።ይህም ማለት **ከቅዱሳን ጋር ባለህግር መሆን ከእንግድነትና ከምጻተኝነት ነጻ መውጣት ማለት ነው።** ኤፌ 2:19 እንግዲያስ **ከእንግዲህ ወዲህ** ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔ ር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም።

## 3. የመንግሥቱ ዜጎች ባህሪያት

በመንፈስ ዳግመኛ የተወለዱ ናቸው። ዮሐ 3፡3-5። በክርስቶስ ጌትነት ስር ይኖራሉ። ሮሜ 14፡17 የመንግሥቱን **ጽድቅ፣ ሰላም** እና **በመንፈ ስ የሆነ ደስታ ይለማመዳሉ** ። እንደ **ፍቅር፣ ፍትህ፣ ትህትና፣ ምሕረት** ያሉ **የመንግሥቱን እ ሴቶችን ያለማመቻመች** ይለማመዳሉ ማቴ 5–7፣ የመንግስቱ ስብከት።በምድር ላይ ያሉ የመንግስቱ አምባሳደሮች/እንደራሴዎች ናቸው።**2ኛ ቆሮ 5፡20**።በዚህ ዓለም ምጻተኞች እና እንግዶች ናቸው። **1ኛ ጴጥሮስ 2፡11** ም ክንያቱም የመጨረሻው መኖሪያቸው በእግዚአብሔር መንግሥት ነውና።

## 4. የመንግሥቱ ዜጎችና መብቶቻቸው

የኃጢአት ስርየት እና ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ አግኝተዋል። ኤፌሶን 1:7 ወደ እግዚአብ ሔር መገኘት እና ተስፋዎች መድረስ ሆኖላቸዋል። **ዕብ 4፡16**። ከክርስቶስ ጋር የዘላለም ርስት ይወርሳሉ። **ሮሜ 8፡17** የአብርሐም ዘር እንደተስፋው ቃልም ወራሾች ናቸው።**ገላትያ 3፡26–28**።የርስታቸው መያዣ በሆነው በመንፈስ ቅዱስ መታተምን አግኝተዋል።**ኤፌ 1:14** የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ወይም ማደሪያ ሆነዋል።**1ቆሮ 3:16-17 2ቆሮ 6:16**

## 5. የመንግሥቱ ዜጎችና ኃላፊነቶቻቸው

ለንጉሱ መታዘዝ **ዮሐ 14:**
**15** "ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ" አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈል ጉ **ማቴ 6፡33**። በዓለም ውስጥ **እንደ ጨው** እና **ብርሃን** ኑሩ **ማቴ 5፡13-**
**16**።ክርስቶስን እንደ አምባሳደሮች በታማኝነት መወከል **2ኛቆሮ5፡20**።ሰወችን መውደድ እና ማገልገል።**ገላ 5፡13**

**ማጠቃለያ፡-**

የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ በክርስቶስ የተቤዣ፣ በአገዛዙ ሥር የሚኖር፣ እና የመንግሥቱን ሙላት ለዘለዓለም እየጠበቀ በዓለም ላይ ሲኖር የመንግስቱን እሴቶች በማንጸባርቅ የሚኖር ሰው ነው። ይህ ማለት የመንግስቱ
ዜጎች ማንነት፣ ታማኝነት እና የወደፊት መዳረሻ የሚወሰነው በምድራዊ መንግስታት ሳይሆን በ እግዚአብሔር ዘላለማዊ አገዛዝ ውስጥ በመሆናቸው ነው ማለት ነው።